# መምሬ ይፍቱኝና ጌታቸው ኃይሌ  የአንድ ሳንቲም ገጽታዎች ታሪክ

ከአቦ አራዳ አባ ሻውል

በአሁኑ ወቅት የኤትዮጵያ ሕዝባዊ የታሪክ ገጽታዎች በምሁራንና በፅንሐተ-ምሁራን መካከል የከረረ ሁኔታ እየተፈጠረ ነው። ይህም ማለት በኢትዮጵያ በኩል ፕ/ር ፍቅሬ ቶለሳ፤ በኤርትራ በኩል ደግሞ ተስፋጺየን አግአዚ በሚል ስያሜ የሚጠራ ግለ-ምሁር። ፕ/ር ፍቅረ ቶለሳና ተከታዮቹ ምሁራን የኢትዮጵያ መጠሪያ ስም መነሻው ኢቶብ ይባላል ሲሉ፤ በኤርትራ በኩል ደግሞ ኤርትራና ኢትዮጵያ የሚባል ስም የለም፤ ስማችን ይላል ግለሰቡ አግአዚያን ነው። በእኔ እምነት እነዚህ ሰዎች ከምሁራን ጎራ ስመድባቸው ፅንሐተ-ምሁራን ግን አይደሉም። በእንግሊዘኛ concept-theory-application ማያያዝ አልቻሉምና ነው። ሁለቱም የሚናበቡብት መስመር ንድፈ-ሀሳብ (ቴዮሪ) እና ተረት-ተረት (ሚቶሎጂ) በማያያዝ ነው።

ፕሮፈሰር ጌታቸው ኃይለን መምህር ብዬ ነው የምጠራቸው ምክንያቱም አሁንም በእንግሊዘኛ mentor ለማለት ነው። ምሁሮቻችን ፕሮፌሶሮችንም ጨምሮ የመምህሮች mentors እርዳታ ተነፍጎዋቸው አልፈዋል። ከአብዮቱ በኃላ ደግሞ አርአያዎች  (role models) ሳያዩ እያረጁ ናቸው። በነገራችን ላይ ቃላቶች የምጠቀምባቸው ሁኔተውና ጊዜያት እየተከተልኩ የምፈጥራቸው ስለሁኑ ለአንባቢያን ግራ ሊገባቸው ይችል ይሆናል። መምህር ጌታቸው ግን የሥነ ጽሑፍ አስተማሪዬ ስለነበሩ ይረዱልኛል ብዬ እገምታለሁ።

መምህር ጌታቸው  በፐ/ሮ ፍቅሬ ቶለሳ መጽሐፍ ላይ ሲያትቱ በታሪክና በተረት ተረት ልዩነትና አንድነት ያላገናዘበ ነው ብለውታል። ትክክል ነው ለዚሁ ነው እኔም በምሁራንና በጽንሐተ-ምሁራን ልዩነት አለ የምለው። የግሪክም ሆነ የአረቦች ሚቶሎጂዎች በኤትዮጵያውያን ሥነ ልቦና ብዙ ሥራ ሰርፀር አልፈዋል። ለዚሁም ብዙ ምክንያቶች ነበሩ።

ለምሳሌ እኔ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እያለሁ፤ የአማርኛ አስተማሪያችን አንድ መጽሐፍ እያነበበልን ዓመቱን ሙሉ አሳለፈ። የመጽሐፉ አርዕስት የራሥ የላሥ የኢትዮጵያ አልጋወራሽ Ras Yelas the prince of Abyssinia። መጽሐፉን በእጃችን ሳንነካው በመስማት ብቻ ታሪኩን በሚገባ አኝከነዋል። ያ ታሪክ ሳይሆን አይቀርም ስደተኛው ሁላ አገሬ አገሬ ኢትዮጵያ የሚያሰኘው። ለካ ታሪኩ የውሸት ነበር። አንድ ሳሙኤል ጆንሶን የሚባል እንግሊዛዊ ለእናቱ መቅበሪያ ገንዘብ ስለአስፈለገው ይህን ተረት ተረት ጽፎ ለእናቱ መቅበሪያ መጽሐፉን ቸበቸበ። ፕ/ር ፍቅሬ ቶለሳም እንደ ሳሙኤል አማራና ኦሮሞን አስታርቃለሁ ብለው እግረ መንገዳቸውም ብር ከሰሩበት እሰየው ነው።

በአንድ በኩል፤ ፍቅረ ቶለሳ የመራ-ራስ ክርስቶስ በኢትዮጵያ መጽሐፍ እንደ መነሻ አድርጎ ካቀረበ ተረት ተረት እንጂ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል። መራ-ራስ ራስ ሳይኖረው መጽሐፉን በገበያ ላይ አውሎ እኔ አንካን በአምስት ብር ብቻ ነው የገዛሁት። የመጽሓፉን ሽፋን የክረስቶስ አድርጎ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ለማዋረድ ካልሆነ በስተቀር ትርጉም ያለው ሽፋን አይደለም።

በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ኤርትራዊ ይሁን ትግራዊ- ኢትዮጵያዊ መሆኑን ያልለየለት ጎረምሳ መሳይ በየእለቱ አዳዲስ አርእስት እያነሳ ወጣቱን ትውልድ እያተራመሰ ይገኛል። አዘውትሮ ሊያነሳው የሚፈልገው ጉዳይ ስለ ID-Politics-Economics ። በሱ ቤት አይዲ ማለት Origin እንደ ፍቅረ ኢትኮፐ እንደሚለው ይመስላል። ሁለቱም ሰዎች ID means investigate and discover መሆኑን ማን በነገራቸው። copy and paste ቢቀርባቸው ይመረጣል።

ተስፋጺየን ስለ ፖለቲካና ኤኮኖሚም ወጣቱን ለማስተማር ይፈልጋል። ዕውቀቱ ሳይኖረው በአባ ሻውል ጨበጣ ብቻ ፖለቲካና ኤኮኖሚክስ ሊያስተምር መሞከሩ ለራሱ ሳይደንቀው አይቀርም፤ በአሁኑ ዘመናችን ገንዘብ የሚካበተው በውሸት ፖለቲካና በቀውጣዊ ንግድ መሆኑን ሳይገባው አልቀረም የሆኖ ሆኖ የያዘው መንገድ የተሳሳተ መንገድ ይመስለኛል። እሱም እንደ ወያኔና ሻዕቢያ ቋንቋን መሰረት በማድረግ ትግሪኛ ተናጋሪዎችን አንድ ላይ ደምሮ ቀንሶ አግአዚያን የሚል ስም ሰጥቶ ከፍቅሪ ቶለሳና ተከታዮቹ ከፍተኛ ጦርነት ለመግጠም ይመስላል። ካዋጣቸውና ሰሚ ካገኙ ሊቀጥሉበት ይችላሉ። ወደ የድንጋይ ዳቦ ዘመን ሊመሉስን ይጥራሉ። ነገደ አማራ፤ ነገደ ኦሮሞ እና ነገደ አግአዚ ለጦርነት ተዘጋጁ። የተቀረነው ደግሞ ለማጨብጨብ እንዘጋጅ።

እኔ ግና ያለፈውን ታሪክ ሳይሆን ለወደፊቱ በምን መንገድ እና ወዴት ለመድረስ እንደሆን ስለሚያስቸግረኝ የታሪክ በተለይም የተረት ተረት በአብዛኛው ከግሪክ የወረስነው ትተን የራሳችን ላይ እናትኩር ባይ ነኝ። እንዴት ለሚለው ጥያቄ እንደሚከተለው አስረዳለሁ።

አንደኛ፤ የኢትጵ እና የአግአዚያን ታሪክ ለታሪክ ጸሐፊዎች ትተን፤ ተረት ተረቱን ደግሞ ለተረተኞች ትተን ሠፊው ሕዝብ ከሺ ዓመታት በፊት ተላቆ የወደፊቱን ኑሮ መኖር አለበት

ሁለተኛ፤ ከሺ ዓመት ርቡን ማለትም የንጉሦች ሚኒሊክ፤ቴዎድሮስ፤ዮውሓንስና የቅርቡ በተረ መንግሥቱን ያስረከቡ አፄ ኃይለ ሥላሴ እንደላይኛው ለታሪክ ፀሀፊዎች ትትን የኤርትራና የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዴት ወደፊት እንዴት እንጓዛለን ለሚለው ምላሽ መስጠት ይኖርብናል።

ጉዞአችን የጀመረው የዛሬ ግመሽ ምዕተ ዐመት ነው። ነገር ግን 50 ዓመት አልበቃ ብሎ ሌላ 50 ዓመት ለችግር እያዘጋጁን ይመስላል። ምክንያቱም እንደሚከተለው ነው።

የሻዕቢያ ግልበጭ ዶ/ር በረኸት ሀብተ ሥላሴ ናቸው

የወያኔ ግልባጭ ፐ/ር መስፍን ወልደ ማርያም ናቸው

የደርግ ግልበጭ አቶ አሰፋ ጨቦ ናቸው

የኢሕአፓ ግልባጭ ደግሞ መምህር ጌታቸው ኃይሌ ናቸው

የእነዚህ ግለታሪከ ምሁራን ሳንቲሙ ተገልብጦ ካልታየና መፍትሔ ካልተፈለገ ወደፊት መራመድ አይቻልም ይሆናል። ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች እንደ ኢትዮጵያውን ወይንም እንደ ኤርትራውያን በልባቸው ስለሚያስቡ የእነሱን ጭንቅላት ማዳመጥ ተገቢ ይመስለኛልና ነው።

ለመሆኑ የሻዕቢያ ግልባጭ ማለት ምን ማለት ነው? ዶ/ር በረኸት በትምህርት፤ በሥልጣን፤ በኃብቻ ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያዊ ነበር። የሻዕቢያ ድርጅት ደግሞ በሁለት ባላ በመንጠልጠል መነሻውና መድረሻው O-D ኤርትራ እንደ መነሻ ኢትዮጵያ እንደ መድረሻ ሲጋዝ ደ/ር በረከት አንዱንም ሳያረጋግጥ ሲታገል ኖረዋል፤ በመጨረሻም አታለሉን በማለት ጉዞውን ደምድመዋል። ትምህርቱም፣ ሥልጣኑም ሆነ ኃብቻው ሳይጠቀምበት አሮበታል።

የወያኔ ግልበጭ ማለትስ ደግሞ ምንድነው? መነሻህን ብቻ በማስታወቅና በማሳየት ጉዞህን መቀጠል ማለት ሲሆን። ፐ/ር መስፍን ወ.ማርያም እስከ ቅርብ ድረስ ማንነታቸውን ሳያሳዩ ግራና ቀኙን እያሉ ለብዙ ዓመታት ስለተጓዙ አሁን በስተ እርጅናቸው ከብዘት-አድዋ መወለዳቸውን አበሰሩን። ወትሮውን የወያኔ ደጋፊ መሆናቸውን ቢነግሩን ለዚህ ሁላ የኤትዮጵያ ምድር መልክአ ምድር አራራችንን በተወጣነው ነበር። የእሳቸው የመልክአ ምድርና የፖለቲካ ጂኦገራፊ ኃላፊ ወይም ባለሙያ ሆነው የወያኔ ድርጅትም በክልል አከላል ጨረሱንና ነው ግልበጭ ያልኩዋቸው።

የደርግ ግልባጭ አቶ አሰፋ ጨቦ ደግሞ፤ ደርግ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የነገረው ወይም የገባለት ቃል አድሐሪያንን ጨርሼ  በተራማጅ ኃይላት ተክቼ ወደ ባራኬ (የጦር ካምፕ) እመለሳለሁ ብሎ በማያውቀው አይዲዮሎጂና በማያውቃቸው ተራማጆች ተታልሎና አታልሎ በመጨረሻው የተዋረደ ድርጅታዎ መሪ ሆኖ አለፈ።

በግልበጩ ደግሞ አቶ አሰፋ ጩቦ እንደ ደርጉ የትግሉ መነሻና ዓላማ O-D ሳያረጋግጡ እንዲሁ በየዕለቱ ፕላንና ዕቅድ እየተመሩ ከየት ተነስተው ወዴት እንደሚደርሱ ገና አሁንም ያልተገለፀላቸው ስለሆኑ የግል ግንኙነታቸውና ዕውቀታቸው እየመነዘሩ በስደት ለመኖር ያቀዱ ይመስለኛል። የኢሕፓ መሪ ጀግና መሪ ብርሃነ መስቀል ረዳ እንደ ጀግንነት አባራሪ ያለውን ልዩነትና አንድነት ሳይገነዘቡ እየጃጁና እያጃጃሉ ይገኛሉ። የወጣቱ አስተማሪ ነኝ እያሉ ደግሞ በየፌስ ቡኩ እየቀለዱ ናቸው። የግለ ሰቦችን የግለ ታሪክ ዘማሪ ይሁኒ እስቲ፤ መምህር ግና አይደሉም።

ወደ እውነተኛው መምህር እንመለስና ፕ/ር ጌታቸው ኃይሌ የታሪክ ምሁር አልነበሩም። እኔን ሲያስተምሩ የአማራኛ መምህር ነበሩ በ1955 አ.ም ከዛ በኋላ ታሪክ አስተመረው እንደሆነ አላውቅም።

የሆነ ሆኖ መምህር ነው የምላቸው ማለትም በእንግሊዝኛ mentor ለማለት ነው። በትግሉ ቋንቋ ደግሞ ጽንኑተ-ምሁር ተብለው ከሚመደቡ ናቸው ወይም ነበሩ። ተራ ምሁርና ፐ/ር አይደሉም። ተራ ምሁር ማት እንደነ በረከት ኃብተ ሥላሴ፤ መስፍን ወ. ማርያም እና አሰፋ ጩቦ የመሳሰሉ ናቸው።

ታዲያ መምህር ጌታቸው ኃይሌ ለምንድን ነው የኢሕአፓ ግልበጭ ያልኩዋቸው። እሳቸው የኤትዮጵያ ጉዳይ ጽንሱንም፣ ንድፈ-ሐሳቡም ሆነ ተግባሩን በሚገባ ስለተረዱና ለዛውም ከፍተኛ የአካል፣ የሥነ አእምሮና የኃይማኖት ግጭት ሳያደናቅፋቸው ፈተናውን ያለፉና እያለፉ ያሉ ስለሆነ ነው።

ለመሆኑ ኢሕአፓ ምንድን ነው? ኢሕአፓ ማለት ኢተኮፕ ነኝ ለሚለው ሆነ አጋዚ ነን ለሚሉ ሁሉም እኔ ማነኝ ለሚሉ መልስ የሠጠ፤ ዓላማውን ምንና የት እንደሆነ የተለመና አካሄዱም በተግባር ያሳየና እያሳዩ ያለ የፖለቲካ ድርጅት ስለሆነ ከመምህር ጌታቸው ኃይሌ ጋር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ናቸው ብዬ አምናለሁ፡፡

O-D መነሻና መድረሻ ለማወቅ ከባድ ነገር አይደለም፤ ከባዱ ነገር መንገዱንና አካሄዱን በአሁኑ ግዜ GPS (Global Positioning System) የሚባል መሣሪያ ስለተፈጠረ ሁላችንም የተራንስፖርት ጉዳይ ቀሎልናል።

የፖለቲካችን ኦና ዲ ግና ከብዶል። በአሁኑ ሰዓት የሁሉም ኢትዮጵያዊና ኤርትራዊ (በአገር ደረጃ ማለቴ ነው) እንጂ በዘር ደረጃማ ኦሮሞው፣ ጉራጌው፣አማራው፣ ትግሬው ወዘተረፈ ማንነቱን ፍለጋ እየዳከረ ይገኛል። መድሻውማ የሌለ ጉዳይ ሆነዋል።

ኢሕአፓና መምህር ጌታቸው የኦና የዲ ችግር የለባቸውም፣ የፕላንና የዕቅድ እንጂ። ሁለቱም ሕዝቡን አንቅተዋል፤ ወዳጁንና ጠላቱን አሳውቀውታል። በኪነታዊ ትግላቸው ኤትዮጵያውነቱንና ማንነቱን በሚገባ አሳምነውታል። ያውም ተረት ተረት ሳይጨምሩበት።

በነገራችን ላይ GPS ማለት ሌላ ትርጉም አለው። አንድ አበሻ ጂፒኤስ የበሽታ አይነት ነው ብሎ

አጫውቶኛል። ሰውዬው በቅርቡ ከኢትዮጵያ የመጣ ነው። በኢንተርነት ጎልጉዬ አግኝቸዋለሁ። አንባቢውም ቢያውቀው ብዬ ነው የጠቀስኩት።

መምህር ጌታቸው ኃይሌ የሚያውቁት ስለ ግዕዝ ብቻ ሳይሆን ስለ ቤተ ክርስቲያን ታሪክም ጭምር ስለሆነ በ ኦና በዲ አባባል ብዙ ሕዝብ ሊያስተምሩ ይችላሉ። በተለይም ደግሞ የኢትዮጵያ አብዮት (የደርግ አብዮት ሳይሆን)።

የኤትዮጵያ አብዮት በነማን እና ለምን እንደተጀመረ ያውቃሉ ብዬ ስለማምን ነው። መምህር ጌታቸውን ለማስታወስ ያክል አራት ኪሎ በሚያስተምሩበት ወቅት የሚከተሉት ተማሪዎችን ያስተውሳሉ ብዬ እገምታለሁ። እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡ ፡

አንደኛ፣ ጌታቸው አርአያና ዮሐንስ ስብሐቱ (ከበለዛና ጉራዕ መንደሮች)

ሁለተኛ፣ ብርሃነ መስቀል ረዳና ዘርዑ ክሕሽን (ከአድዋና አጋሜ አውራጃዎች)

ሶስተኛ፣ ዮሐንስ ብርሃኔና ፀጋየ ገብረ መድህን (ከአገረ- ሁሉ አሞክሩ ወዘሰናዬ አፅንኡ)

የእነዚህ ሰዎች ታሪክ እውነተኛ የኤትዮጵያ አብዮት ታሪክ ነበር ነውም።

ከዚህ ተነስተን ታሪክ ማለት የወደፊቱ የልጆቻችን ዕድል ለማስተላለፍ ብንሞክር ምንኛ ባማረብን ነበር። ለልጆጃችን መነሻና መድረሻችን የእውነተኛ አብዮት ትክክለኛውን ማሰየት ነው እንጂ የከሸፈውንና እየከሸፈ ያለውን አብዮት አልነበረምና አይደለምም ብለን ወጣቱን ማስተማር ይጠበቅብናል።

የኤትዮጵያውያን የማንነት ታሪክ የፕሮፌሰር ዲለቦ ገ. ላፒሶ ያለፉበት የግል ታሪክ በቂ ማስረጃ በሆነ ነበር።